ይልቁንም ተማርከው ፋርስ ባቢሎን ከወረዱት አይሁድ መካከል ሠለስቱ ደቂቅ ጽኑ መከራ ወዳለበት ወደ እቶነ እሳት ተጥለው ነበር:: ይሁን እንጂ ተባርዮን የማያስቀር ጌታ ከሰባው ዘመን በኋላ በዓይነ ምሕረት ስለጎበኛቸው በሚያቃጥለው እሳትና በሚያስጥመው ውኃ መካከል አሳልፎ ወደ ዕረፍተ ኢየሩሳሌም አውጥቷቸዋልና ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ይህን አለ:: ይህም ቃለ ውዳሴ ከሃሌ ኩሉ (ሁሉን ቻይ) የሆነው እግዚአብሔር "ዘአንበለ እሳተ አንደደ፤ ወዘአንበለ ማየ አብረደ፤ ሰብአ ትካትን ያለ እሳት በውኃ አጠፋ፤ ሰብአ ሰዶምን ያለ ውኃ በእሳት አጠፋ"[144] ተብሎ እንደተነገረለት ያለ እሳት ማንደድ፤ ያለ ውኃ ደግሞ ማብረድ የሚችል ኃያል አምላክ በመሆኑ በኋለኛው ዘመን ሊፈጽመው ያለውን የድኅነተ ዓለም ሥራ አስቀድሞ በምሳሌ የገለጠበትና በትንቢት ያሳየበት መጽሔተ ምሥጢር ነው::

ሦስተኛውና የመጨረሻው ምሥጢራዊ ትርጓሜ ደግሞ እስራኤል ዘሥጋ ወደ ምድረ ግብፅ መሰደዳቸው፣ ኋላም ወደ ፋርስ ባቢሎን ተማርከው መውረዳቸው ነፍሳት በሠራዊተ ዲያብሎስ ተማርከው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት ወደ ሲኦል ገሃነም ለመውረዳቸው ምሳሌ ነው:: ሕዝበ እስራኤል ጽኑ መከራ ወዳለበት ወደ ምድረ ግብፅና ወደ ባቢሎን በመውረዳቸው ምክንያት አሕዛብ እንደሰለጠኑባቸው ሁሉ፤ ነፍሳትም ወደ ገሃነም በመውረዳቸው ሠራዊተ አጋንንት ሰልጥነውባቸዋል:: በመሆኑም ነፍሳት በርደተ ገሃነም ምክንያት መከራ ነፍስ በጸናባቸው ጊዜ "ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ:: እማንቱ ይምርሃኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ፤ ብርሃነ ሕይወት የሚሆን የባሕርይ ልጅህ ወልድን፣ አንድም መንፈሰ ጽድቅ የሚሆን የባሕርይ ሕይወትህ መንፈስ ቅዱስን ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት መርተው ያገቡን ዘንድ ላክ" (መዝ. 42÷3)፤ "ፈኑ እዴከ እምአርያም፤ ክንድህ የሚሆን ልጅህን በሥጋ ላክ::" (መዝ. 143÷7-8)፤ "እንሥእ ኃይለከ ወነዓ አድኅነነ:: አምላከ ኃያላን ሚጠነ:: አብርህ ገጸከ ላዕሌነ ወንድኀን፤ ኃይልህ የሚሆን የባሕርይ

[144] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 286-287::



ልጅህን በሥጋ ገልጸህ አድነን:: የኃያላኑ ባለቤት አቤቱ ከሲዖል፣ ከገሃነም ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት መልሰን:: ገጸ ምሕረትህን ገልጸህ አንድም ሰው ሆነህ አድነን::"[145] (መዝ. 79÷2-3)፤ እያሉ በጮኹ ጊዜ ቸርና መሐሪ የሆነው አምላክ ብርሃናዊ መልአኩን ወደ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ልኮ በብሥራተ መልአክ ተፀንሶ ተወለደ:: በዚህም ረቂቅና ድንቅ የሥጋዌ ምሥጢር ወደ ገሃነም ተማርከው የወረዱ ነፍሳትን ወደ ዕረፍት ገነት መንግሥተ ሰማያት አውጥቶአልና ነቢየ እግዚአብሔር "አኀለፍከነ ማዕከለ እሳት ወማይ፤ ወአውጻእከነ ውስተ ዕረፍት" በማለት ገልጾ ተናገረ::

ከላይ እንደተረጎምነው በባቢሎን እሳት ውስጥ ተጥለው የነበሩት ሠለስቱ ደቂቅ በእሳቱ ጉድጓድ ሆነው በስድስት አንቀጽ መላልሰው ያመሰገኑት ምስጋና ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ መድኅን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣና ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን የሚያጠይቅ እንደሆነ ተመልክተናል:: ከዚህም ጋር ልናስተውለው የሚገባው ሌላው ዐቢይ ምሥጢር ደግሞ ሠለስቱ ደቂቅ በስድስት አንቀጽ ወስነው ካቀረቡት ምስጋና አያይዘው በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ፈጣሬ ዓለማት፣ እምዳኤ ዓለማት፣ ወመጋቤ ፍጥረታት የሆነውን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርን እርሱ ባወቀ ገንዘብ እንዴት እንደሚያመሰግኑትና እንደሚገዙለት በመግለጥ ሠላሳ ሦስት ጊዜ መላልሰው አመስግነዋል:: የዚህ ምስጋና ትርጓሜ ምሥጢርም በስድስተኛው ወር በብሥራተ መልአክ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም የሚወለደው የባሕርይ አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በዚህ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ተመላልሶ እንደሚያስተምርና በመጨረሻም ለድኅነተ ዓለም ሲል በፈቃዱ ሕይወቱን ቤዛ መሥዋዕት አድርጎ እንደሚሰጥ የሚያስረዳ ነው::[146]

[145] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 230፣ 404-405፣ 653::

[146] ድርሳነ ሚካኤል፣ (አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1989 ዓ.ም.) ገጽ 115-117::

ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን የተሰኘው ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ «ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት» (ገላ. 4÷4) ወፍቁረ ሰብእ የሆነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ለአባታችን ለአዳም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ የሰጠው የተስፋ ድኅነት ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከባሕርዩ የወለደውን፣ በመልክ የሚመስለውንና በባሕርይ የሚተካከለውን አንድያ ልጁን ሂድ፣ ውረድ፣ ተወለድ፣ ተሰቀል፣ሙት ብሎ ወደዚህ ዓለም ላከው፤ ከሔዋናዊት ድንግልም ተወለደ ብሎ እንደተናገረው በመልአከ ብሥራት በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት የድኅነተ ዓለም የምሥራች ከሁሉ በፊት ለእመቤታችን ተሰብኳል::

በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ እንደተጻፈው መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር በነገራት ጊዜ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ሁለንተናዊ ሕይወቷን በንጽሕናና በቅድስና በድንግልናም ለእግዚአብሔር ክብር የሰጠች መሆኗን በመግለጥ "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" (ሉቃ. 1÷34) አለችው:: በዚህም ቃለ አውሥኦ መሠረት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሥጋዊ ምኞትም ሆነ የዚህን ዓለም ከንቱ ነገር በማሰብ፣ በመናገርና በመሥራትም ፈጽማ የማታውቅ ድንግል በክልኤ (በሥጋም በነፍስም ድንግል) መሆኗን መስክራለች::

መልአኩም መልሶ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል÷ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» (ሉቃ. 1÷35) ሲል ነግሮአታል:: በዚህም ወልደ እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ ሰው የመሆኑ ምሥጢር በግብረ መንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ረቂቅና ድንግቅ ምሥጢር መሆኑን በመግለጥ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ፣ እመ እግዚአብሔር መሆኗን አረጋግጦአል::[147] በመጨረሻም ቅድስት ድንግል

(147) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 17.



እመቤታችን «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም::» (ሉቃ. 1÷37) የሚለውን ቃለ መልአክ በእምነት ተቀብላ «ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ አለች::» (ሉቃ. 1÷38) በዚህን ጊዜም ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀኗ ተቀርጿል (ተፀንሷል)::

በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስናቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ገጸ ንባባት በቅጥነተ ኅሊና ሲመረመሩና በስፍሐ አእምሮ ሲታዩ ረቂቅና ድንቅ፣ ጥልቅና ምጡቅ የሆነ የምሥጢረ ድኅነት መድበል አላቸው:: ይኸውም በመጀመሪያ መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ተልኮ ሲመጣ ያቀረበው ልዩ ሰላምታና ውዳሴ፤ እንዲሁም ከድንግል ማርያም ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ (ሉቃ. 1÷26-39) አስቀድሞ ወደ ካህኑ ዘካርያስ በተላከ ጊዜ እንደገሠጸውና እንደተቆጣው ያይደለ በፍጹም ትሕትናና ደስ በሚያሰኝ ቃለ ውዳሴና ቃለ አክብሮ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን እንዳበሠራት ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በግልጥ ይመሰክራል:: ይኸውም ምንም እንኳን እመቤታችን መልአኩን እየመላለሰች ብትጠይቅም ቅሉ ቀደም ሲል በዘካርያስ ላይ ተቆጥቶ እንዳደረገው በእርሷ ላይ ግን አንዳችም ነገር አላደረገም:: ይልቁንም መጽሐፍ «... ደመና ብሩህ ዘከለላ፤ ወልአከ በሰላም ተናገራ፤ ወይቤላ ተፈሥሒ ፍሥሕት ቡርክት አንቲ እምአንስት»[148] እንዳለ በፍጹም ትሕትና ሆኖ በምስጋና ቃል መለሰላት እንጂ::

የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም መጻሕፍት በስፋት እንደሚያስረዱን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል መድኅነ ዓለም ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና እንደምትወልደው ባበሠራት ጊዜ «እምአይቴ ሊከውን ዘከመዝ ብሥራቱ፤ ዘእንበለ ምት እምድንግል ጽንሰት፣ ወዘእንበለ ዘር እምድር ዕትወ፤ ሴት ያለ ወንድ፣ ምድር ያለ ዘር ፍሬን ማስገኘት ይችሉ ዘንድ

(148) «መቅድመ ኪዳን»፣ *መዝሙረ ዳዊት ወመዝገበ ጸሎት፣* (አሥመራ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት 1984 ዓ.ም.) ገጽ 597::

እንደዚህ ያለውን የምሥራች ከወዴት አገኘሽው?»(149) ስትል ጠይቃዋለች። በዚህም ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን ምክረ ከይሲን ያለምንም ጥያቄና ቅድመ ሁኔታ ተቀብላ የፍዳና የመርገም፣ የሞትና የመከራ ምክንያት ከሆነችው ከቀዳሚት ሔዋን ፈጽማ የተለየች እንደሆነች ይገነዘቧል።

በኦርቶዶክሳውያን አበው ትውፊት መሠረት ቅድስት ድንግል ማርያም ብሥራተ መልአክን የሰማችውና የተቀበለችው ሐርና ወርቅን እያስማማች ስትፈትል ከነበረችበት ከቤተ መቅደስ ውስጥ ሆና ነው። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይህንን አስመልክቶ ሲናገር «ወእንዘ ትፌትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ፤ ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ሆና ሐርና ወርቅን እያስማማች ስትፈትል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በድንገት ታያት»(150) ብሏል። ዳግመኛም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዳመሠጠሩትና እንደተረጐሙት ሐርና ወርቅ በእመቤታችን እጅ መስማማታቸውና አንድ መሆናቸው መለኮትና ትስብእት በመንፈስ ቅዱስ ግብር አማካይነት በማኅፀኗ ፈጽመው ለመዋሐዳቸው ምሳሌ ነው።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጽጌ ድንግል ይህንን ዐቢይ ምሥጢር ሲገልጽ «ፈትለ ወርቅ ወፈትለ ሜላት አመ በአጽባዕትኪ ተባየጹ፤ አምሳለ መለኮት ወትስብእት እንዘ ኢየሐፁ፤ ተአምረ ብርሃን ማርያም ለፀሐየ ጽድቅ እንቀጹ፤ ጸገዱኪዮ እንበለ አብ በሰሚዐ ቃሉ ወድምፁ፤ ለገብርኤል መልአክኪ ዘፍሡሕ ገጹ፤ የሐርና የወርቅ ፈትል በጣቶችሽ ውስጥ እንደተስማሙና እንደተዋሐዱ መለኮትና ትስብእት በማኅፀንሽ ፍጹም ለመዋሐዳቸውና አንድ

(149) ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 171።

(150) *መጽሐፈ ልደታ፣ ["The Book of the Nativity of St. Mary"]*, ed. M. Chaine, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium*, vol. 7, *Scriptores Aethiopici,* ገጽ 9-10። አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 612-613። Metropolitan Anthony, "Mary in the Orthodox Tradition," *Mary in the Church*, ed. John Hyland (Athlone: Veritas Marist Brothers, 1989), 98-99. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 89, 206. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 169-171፣ 385።





**ሥዕል 5፡- መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበሥራት**

«ወእንዘ ትፌትል ወርቀ ወሜላተ፤ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ።»

(መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 171)

«ፈትለ ወርቅ ወፈትለ ሜላት አመ በአፅባዕትኪ ተባየጹ፣ አምሳለ መለኮት ወትስብእት እንዘ ኢየሐፁ፤ ተአምረ ብርሃን ማርያም ለፀሐየ ጽድቅ እንቀጹ፤ ጸገዱኪዮ እንበለ አብ በሰሚዐ ቃሉ ወድምፁ፤ ለገብርኤል መልአክኪ ዘፍሡሕ ገጹ።»

(ማኅሌተ ጽጌ፣ ገጽ 612-613)

ለመሆናቸው አማናዊ ምሳሌ ሆነ:: ብርሃነ ቅዱሳን ለሆነው አማናዊው ፀሐየ ጽድቅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ደጃፉ የሆንሽ፣ ተአምርሽ የበዛ ድንግል ማርያም ሆይ 'ናሁ ትፀንሲ' የሚለውን የመልአከ ሰላም የቅዱስ ገብርኤ ልን ቃለ ብሥራት 'ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ' ብለሽ በመቀበልሽ ብርሃነ ቅዱሳን የሚሆን ክርስቶስን ያለ አባት በኅቱም ድንግልና አስገኘሽው»[151] በማለት ተናግሮአል::

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት በእመቤታችን አማካይነት የተከናወነው የሥጋዌ ምሥጢርም ሆነ ከእርሷ በተነሣው ሥጋና ነፍስ የተፈጸመው አማናዊ የድኅነተ ዓለም ሥራ የሦስቱም አካላት ምክር ማለትም የሥላሴ ፈቃድና ሥምረት ነው:: ይህ መሠረተ እምነት ከነገረ ድኅነት ትምህርት ጋር የተያያዘ ጥልቅ ምሥጢር አለው:: በሌላ አገላለጽ በዘመነ ሥጋዌ በአካላዊ ቃል በእግዚአብሔር ወልድ በኩል የተደረገው አምላካዊ የማዳን ሥራ [Redemptive Deeds] ሐዲስ ተፈጥሮ [Recreation] ይባላል::

በመሆኑም ይህ ተፈጥሮ ሐዲስ መባሉም የሰው ልጅ በጥንተ ተፈጥሮ [Creation] የተሰጠውን የእግዚአብሔር መልክ በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት ስላቆሸሸና ንጽሐ ጠባዩን ስላሳደፈ፤ በዚህ ረቂቅና ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር ምክንያት አጥቶት የነበረውን ጸጋና ክብር እንዲሁም የልጅነት ሥልጣን ዳግመኛ ስላገኘበት ነው::[152] በመሆኑም መጽሐፍ «ይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር::» (ዘፍ. 1÷26) ብሎ እንደመሰከረው የሰው ልጅ ጥንተ ተፈጥሮ በሦስቱም አካላት ፈቃድና ሥምረት እንደተከናወነ ሁሉ፤ እንዲሁም

(151) አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 612-613::
(152) አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ»፣ ገጽ 544:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], *«መጽሐፈ ምሥጢር» ["The Book of Mystery"],* ገጽ 88:: አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 613:: Metropolitan Anthony, "Mary in the Orthodox Tradition," 98. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 17, 83.



የሰው ልጅ ሐዲስ ተፈጥሮ ፈጣሬ ፍጥረታት በሆኑት [The Original Author of Creation] በሦስቱ አካላት ፈቃድና ሥምረት መፈጸሙ የግድ ነው:: ሌላው ምሥጢር ደግሞ ወልደ እግዚአብሔር ከእመቤታችን በተዋሕዶ ሰው ሆኖ በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈጸመው የድኅነተ ዓለም ሥራ (ሐዲስ ተፈጥሮ) በዕለተ ዓርብ መከናወኑ፤ በጥንተ ተፈጥሮ በዕለተ ዓርብ በአርአያ ሥላሴ ለተፈጠረው የሰው ልጅ የተደረገ አምላካዊ መግቦት /የቸርነትና የቤዛነት ሥራ/ መሆኑን በምሥጢር ያመለክታል::

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በቅድስት ሥላሴ ምክር መሠረትነት የሰው ልጆች ሐዲስ ተፈጥሮ የተፈጸመበትን የሥጋዌ ምሥጢር በተናገረበት አንቀጽ:- «አስተርአየ በፈቃዱ፤ ወበሥምረተ አቡሁ፤ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኃነነ፤ በእርሱ ፈቃድ፣ በአባቱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ ሰው ሆኖ አዳነን»[153] በማለት መስክሮአል:: ከዚህ ዓውደ ንባብ ድኅነተ ዓለም ራሱ ሐዲስ ተፈጥሮ በመሆኑ ለጥንተ ተፈ ጥሮ መሠረት የሆኑ ሥላሴ የዚህ ሐዲስ ተፈጥሮም (ምሥጢረ ድኅነት) መሠረት መሆናቸውን ይገነዘቧል:: ስለሆነም «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል÷ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::» (ሉቃ. 1÷35) የሚለው ቃለ መልአክ በዚህ ድንቅ ምሥጢር አማካይነት ተፈጽሟል፣ ታትሟል፣ ተደምድሟል::

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ ርእሰ ምሥጢራት ተብሎ በሚጠራውና በሚታወቀው በምሥጢረ ሥጋዌ እምነታችንና ትምህርታችን መሠረት የወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ሰው የመሆን ምሥጢር የተፈጸመውና ወልደ እግዚአብሔር ወልደ ማርያም የሆነው በኃይለ መንፈስ ቅዱስ፣ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ምክንያቱም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደውን ቀዳማዊ አምላክ፤ ድኅረ ዓለም ያለ አባት በኅቱም

(153) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 47::*

ድንግልና ፀንሳ፣ በኋቱም ድንግልና ለመውለድ የቻለችውና የበቃችው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሆኑ ነው:: አብሣሪዋ የሆነው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል» ያላትም ስለዚህ ነው:: ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ይህንን ረቂቅ ምሥጢረ ትሥጉት አስመልክቶ በተናገረበት አንቀጽ «ውእተ ጊዜ ትቤ ነዮ አመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ:: ወሶበ ትቤ ዘንተ ወልደ እግዚአብሔር ኮና ወልደ በምጽአተ መንፈስ ቅዱስ፤ ወይእቲኒ ኮነት እመ በኃይለ ልዑል:: እመሰ ኢጸለላ መንፈስ ቅዱስ ወኃይለ ልዑል እምኢክህለት አግምሮቶ ለወልደ ልዑል»(154) በማለት አብራርቶና አፍታቶ ተናግሯል::

ዳግመኛም በዕለተ ብሥራት የተገለጠውን የርደተ መንፈስ ቅዱስ ምሥጢር አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም መጽሐፍ:-

> ወናሁ ሰማዕነ እምአፈ ገብርኤል መልአክ ዘከመ ይቤላ ለማርያም መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ፣ ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ፤ ወይሰመይ ወልደ ልዑል:: አኮ ዘመጽአ ላዕሌሃ መንፈስ ቅዱስ ዘከመ መጽአ ላዕለ ነቢያት ወሐዋርያት ወላዕለ ኵሎሙ መሃይምናን ለቀድሶ ነፍሶሙ ወለአንጽሖ ሥጋሆሙ፤ ወለአጽድቆቶሙ ወለአብኦቶሙ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ባሕቲቱ::(155) ይላል::

የዚህ ኃይለ ቃል ፍቼውም እነሆ ከመልአኩ ከቅዱስ ገብርኤል ቃል ድንግል ማርያምን መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህም ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ እንደነገራት ሰማን:: መንፈስ ቅዱስ በእመቤታችን ላይ ማደሩም በቅዱሳን ነቢያትና በቅዱሳን ሐዋርያት እንዲሁም በምእመናን ሁሉ ላይ ነፍሳቸውን ለመቀደስ፣

(154) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *«መጽሐፈ ምሥጢር» ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 88::

(155) አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ»፣ ገጽ 548:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 15, 40, 166.



ሥጋቸውን ለማንጻት ብሎም ለማጽደቅና ወደ መንግሥተ ሰማያት ለማስገባት እንደመጣው ዓይነት አይደለም::

ከዚህም ጋር የብሥራተ መልአክን ትርጓሜ ምሥጢር የሚያትተውና የሚያብራራው የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ድርሳን ይህን ገጸ ንባብ ከዚህ እንደሚከተለው ያትታል::

> ለማርያምሰ እምከርሠ እማ ቀደሳ ወአንጽሐ መንፈስ ቅዱስ በቅዳሴ ወንጽሕ ዘኢይትነገር:: ወአመ ሥጋዌሁ ለወልደ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መጽአ ላዕሌሃ ከመ ይኩን ፅንሳ እምውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ:: ወኢተፈልጠ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ እምላዕሌሃ ኢአሐተ ሰዓተ፤ ወኢቀጽበተ ዓይን ለዓለመ ዓለም ይሄሉ ምስሌሃ እንበለ ተፈልጦ::(156)

ይህም ማለት ድንግል ማርያምን ግን መንፈስ ቅዱስ ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር በማይቻል ንጽሕናና ቅድስና አከበራት፣ ቀደሳት፣ አነጻትም:: የእግዚአብሔር አብ ልጅ ከእርሷ ሰው በሆነ ጊዜም መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ፅንሷ ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ በኋቱም ድንግልና ይሆን ዘንድ ነው:: ይህ ቅዱስ መንፈስም ለአንዲት ሰዓት ወይም ለዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳ ከእርሷ አልተለየም:: ይልቁንም ከእርሷ ሳይለይ ለዘላለሙ ይኖራል እንጂ በማለት አብራርቶና አፍታቶ ይናገራል::

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ የነገረ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት [Pneumatology] የነገረ ማርያምና የነገረ ሥጋዌ አስተምህሮ መሠረትና የአምላካውያት ምሥጢራት ሁሉ መግቢያ በርም ነው:: ["Pneumatology is the locus of entry in to the divine mysteries of God."] ለአብነት ያህል ብንጠቅስ በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን በጎበኘቻት ጊዜ ኤልሳቤጥ

(156) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 40.

ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተመልታና ቃሏን ከፍ አድርጋ አሰምታ፡- «ወምንትኑ ዝንቱ ከመ ትምጻእ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ፤ የጌታዬ እናቱ እመቤቴ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድር ነኝ?» (ሉቃ. 1÷43) ስትል ተናግራለች። ከዚህም ኃይለ ቃል ከሣቴ ምሥጢር የሆነው መንፈስ ቅዱስ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር በቅድስት ኤልሳቤጥ አድሮ ለዓለም ሁሉ መግለጡንና ማረጋገጡን ልብ ይሏል።

ይኸው ቅዱስ መንፈስ በቅዱሳን ሐዋርያትም አድሮ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ገልጦአል። ለዚህም «እርሱም፡- እናንተ ስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ÷ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ» (ማቴ. 16÷15-17)፤ «ስለዚህ ማንም... በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፡- ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ ስንኳ እንዳይቻል አስታውቃችኋለሁ።» (1ኛ ቆሮ. 12÷3) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎችና ምስክሮች ናቸው። ስለሆነም እነዚህ ገጸ ንባባት የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በሥጋዊና በደማዊ አእምሮ ማወቅና መረዳት ወይም ደግሞ ከሥጋዊ ከደማዊ መምህር መገንዘብ እንደማይቻል ያመለክታሉ። ዳግመኛም በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ካልሆነ በቀር መድኅነ ዓለም ክርስቶስን አምላክ፣ ወልደ አምላክ ብሎ ማመንም ሆነ ማሳመን ለማንም እንደማይቻል በግልጥ ይመሰክራሉ።

ከላይ በዝርዝር እንደለጥነው የድኅነታችን ምሥጢር የተፈጸመበት አምላካዊ የቸርነት ሥራ በማኅፀነ ድንግል የተከናወነው በግብረ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተመልክተናል። የድኅነታችን ምክንያት የሆነችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም ከመልአከ ብሥራት ከቅዱስ ገብርኤል አንደበት የሰማችውንና በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና



ጥበብ በእርሷ ሕይወት የሚፈጸመውን የወልደ እግዚአብሔርን ድንግልናዊ ጽንስና ልደት አምና መቀበሏን «ነየ ዓመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ የእግዚአብሔር ገረዱ እነሆኝ አለሁ፤ እንዳልክ ይሁንልኝ፤ እንደቃልህም ይደረግልኝ» (ሉቃ. 1÷38) በማለት ገልጻ ተናግራለች። ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንትም ይህ የእመቤታችን ቃለ ተአምኖና በጎ ፈቃድ ለአካላዊ ቃል ሰው መሆንና ለድኅነተ ዓለም ሥራ ወሳኝ መሆኑን መላልሰው አስተምረዋል። ከዚህም ጋር ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀነ ድንግል በመቀረጹ ይህ የእመቤታችን መልካም ፈቃድ ለነገረ ድኅነት መሠረት መሆኑንም ይገነዘቧል።

መልአከ እግዚአብሔር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር በሁለት ዓይነት መንገድ ገልጾ መስክሮአል። ይኸውም በመጀመሪያ መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን «... ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።» (ሉቃ. 1÷35) ሲል ከእርሷ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና የሚወለደው መድኅን ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በግልጥ አስረድቷል።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ግሩምና ድንቅ በሆነው በመድኅነ ዓለም በኢየሱስ ክርስቶስ ድንግልናዊ ፅንስና ልደት የጥርጥር ጭጋግ በኅሊናው የተፈጠረበትና የተጋረደበት አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ የምሥጢሩን ርቀትና ጥልቀት መረዳት በተሳነው ጊዜ መልአከ እግዚአብሔር በሕልም ተገልጦ እንዲህ አለው፡- «የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ÷ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመወሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ÷ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል።

ትርጓሜውም:- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ የሚል ነው።» (ማቴ. 1÷20-23) ይህ ቃለ መልአክ ከድንግል ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ የሚወለደው መሲሕ አስቀድሞ ትንቢት የተነገረለትና ሱባኤ የተቆጠረለት የባሕርይ አምላክ መሆኑን ያስገነዝባል።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ከላይ የገለጥነውንና ሰማያዊው የእግዚአብሔር መልአክ የሰጠውን አማናዊ ምስክርነት ሲያነጻጽር «ወአክበራ ዮሴፍ ከመ እግዝእቱ ወተቀንየ ላቲ ከመ ገብር። ወበእንተዝ አብሠራ መልአክ ለቅድስት ድንግል ማርያም ከመ ትትፌሣህ ወሎቱኒ ከመ ኢይደናፍቅ»(157) ብሏል። የሊቁ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢር አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር ከመልአኩ እንደበት በጎላ በተረዳ ነገር ካወቀ በኋላ ድንግል ማርያምን እንደ እመቤቱ አድርጎ አከበራት፤ እንደ አልጋይም ሆኖ ታዘዛት። በዚህም መሠረት አንዱ የእግዚአብሔር መልአክ ለሁለቱም ማለት ለእመቤታችንና ለዮሴፍ ተገለጠ። ድንግል ማርያምን ደስ ይላት ዘንድ አበሠራት፤ ቅዱስ ዮሴፍን ግን የጽንሷን ነገር እንዳይጠራጠር ምሥጢሩን ገልጾ አስረዳው ማለት ነው።

እስካሁን ድረስ እንዳየነው የቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተ ምህሮ ዐቢይ መሠረት መሆኑን ተመልክተናል። ልበ አምላክ የተባለው ቅዱስ ዳዊት ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና የሆነችው እመቤ ታችን ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ልዩ መሣሪያ ሆና መመረጧን ሲናገር «... ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን፤ እምኵሉ ተ ዓይኒሁ ለያዕቆብ። ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር» (መዝ. 86÷2-3) በማለት መስክሮአል።

(157) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], *«መጽሐፈ ምሥጢር» ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 9-10። St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 38, 60. Meersseman trans. *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 41.



ኢትዮጵያውያን መተርጉማን ይህንን ቃለ ትንቢት ለምሥጢ ረ ሥጋዌ ሰጥተው ሲተረጉሙ «ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከቤተ ያዕቆብ ደናግል ይልቅ በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችንን ሕዋሳት ለተዋሕዶ መረጠ፣ ወደደ። ዳግመኛም ኃያሉ አምላክ በእርሷ ሕይወት የሠራው ልዩ ሥራ ማለትም በኅቱም ድንግልና ፀንሳው፣ በኅቱም ድንግልና እንድትወልደው የማድረጉ ምሥጢር ዕፁብ ድንቅ በመሆኑ እንበለ ዘርዕ፣ እንበለ ሩካቤ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ በእውነት ሀገረ እግዚአብሔር ተብለሽ ልትጠሪ ይገባሻል»(158) እያሉ አብራርተው ገልጸዋል።

ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ አስመልክቶም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ራሷ የነገረ ማርያም ሲቃውንት «መዝሙረ ድንግል፣ ጸሎተ ማርያም» እያሉ በሚጠሩት ምስጋናዋ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሤት ታደርጋለች፤ ... ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና» (ሉቃ. 1÷47-49) በማለት ተናግራለች። ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳን አበው መፍቀሬ ሰብእ የሆነው አምላክ በልዩ አምላካዊ ጥበቡ ባደረገው የሥጋዌ ምሥጢር አማካይነት የፈጸመውን የድኅነተ ዓለም ሥራ ታላቅነትና አስደናቂነት ሲገልጡ «ልዑል እግዚአብሔር ይህንን ዓለም ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ሰው ሆኖ ይህንን ዓለም ያዳነበት ጥበቡ እጅግ ይበልጣል» ብለዋል።

ይህ ኃይለ ቃል በሌላ አገላለጽ ሲነገር ፈጣሬ ዓለማት የሆነው ኃያሉ እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በጥንተ ተፈጥሮ ከፈጠረበትና ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ካስገኘበት ጥበቡና ክሂሎቱ (ችሎታው) ይልቅ በኋለኛው ዘመን ለቤዛ ዓለም፣ ለድኅነተ ዓለም ሲል ከእመቤ ታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ይህን ዓለም ዳግመኛ

(155) *መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 432። ቅዱስ ያሬድ፣ *ዝማሬ መዋሥዕት*፣ ገጽ 125። ቅዱስ ሳዊሮስ፣ «በእንተ ሃይማኖተ ኒቅያ»፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 357፣ 361። ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 403። ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 16-17።

በሐዲስ ተፈጥሮ የፈጠረበትና ያዳነበት የሥጋዌ ጥበቡ እጅግ ይበል ጣል፣ ይደንቃል ማለት ነው:: ስለሆነም በእመቤታችን በኩል የተደ ረገው ይህ አምላካዊ ጥበብና አድኅኖት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ልዩ ድርሻ ያስገነዝባል፣ ያረጋግጣልም::

በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋናም ይህንን ምሥጢረ ተዋሕዶ ሲያደንቅ «አንቲ ተዓብዪ እምብዙኃት አንስት:: እስ ነሥኣ ጸጋ ወክብረ:: ኦ ማርያም ወላዲተ አምላክ ሀገር ወንፈሳዊት ዘኀደረ ባዕሴሃ እግዚአብሔር ልዑል፤ ድንግል ማርያም ሆይ ጸጋና የክብር ክብር ካላቸው ከብዙ ሴቶች አንቺ ትበልጫለሽ:: አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ ልዑል እግዚአብሔር ያደረብሽና የከተመብሽ ረቂቅ ከተማ ነሽ::»(159) ይላል:: በዚህም ቃለ ውዳሴ መሠረት እመቤ ታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሀገረ እግዚአብሔር መባሏ ንጉሥ በከተማው እንዲኖር፤ በባሕርዩ ሞት ሽረት፣ በመንግሥቱ ኅልፈት የሌለበት ሰማያዊውና ዘላለማዊው ንጉሥ ክርስቶስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማኅፀኗን ዓለም አድርጎ ስለኖረባትና ስላደረባት ነው:: ይህ ሁሉ አምላካዊ የቸርነት ሥራም ባሕረ ምሕረት ወደብረ ትዕግሥት የሆነው አምላክ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በመልኩ የፈጠረውን የሰውን ልጅ ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ ለማደስና ለመቀደስ ብሎም ለማክበር በፈቃዱ ያደረገው አምላካዊ መግቦትና ወይም የድኅነት ጉዞ ነው::

ዳግመኛም በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በስፋት የሚታወቀው የድንግል ማርያም ውዳሴ «ዛቲ ይእቲ ኢየሩሳሌም ሀገሮሙ ለነቢያት ወማኅደ ረ ፍሥሓሆሙ ለኲሎሙ ቅዱሳን፤ የቅዱሳን ነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ይህቺ እመቤታችን ናት:: የቅዱሳን ጻድቃን፣ የቅዱሳን ሰማዕታት፣ የቅዱሳን መላእክት ደስታቸው የሚሆን የጌታ ማደሪያም የምትሆን እመቤታችን

(159) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 154:: ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ገጽ 55፣ 174::* St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 37, 44. Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*, 244.



ድንግል ማርያም ናት»(160) በማለት ዓውደ ንባቡን በምሥጢር ተርጉሞ ገልጿል፣ አጽንቶአል:: በመሆኑም ኢየሩሳሌም ማለት በቁሙ ሲተረጎም ሀገረ ሰላም ማለት እንደሆነ ሁሉ፤ አማናዊቷ ኢየሩሳሌም እመቤታ ችንም የንጉሠ ሰላም የክርስቶስ ማደሪያው ሀገሩ፣ መቅደሱ፣ ዙፋኑ ናትና:: ይህንንም የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍተ ውዳሴያትና ቅዳሴ ያት «ሰማይ ዳግሚት ብኪ ድኅነ ዓለም ወበወልድኪ ኮነ ሰላም፤ ሁለተኛ ሰማይ ድንግል ማርያም ሆይ በአንቺ ምክንያትነት ዓለሙ ሁሉ ዳነ፤ በልጅሽም ፍጹም ሰላም ሆነ»(161) በማለት ይመሰክሩላታል::

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ከፍጡራን ሁሉ በላይ ሆና የአምላክ እናት የመሆን ልዩ ጸጋ የተሰጣትና በዚህም አምላካዊ ጸጋ ቅድስተ ቅዱሳን፣ ንጽሕተ ንጹሐን፣ ክብርተ ክቡራን፣ ልዕልተ ልዑላን የሆነችው እመቤታችን ድንግል ማርያም ብቻ ናት:: ስለሆነም ታላቅ አምላካዊ ጸጋና ልዩ ምርጫ ምክንያት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከሰማያውያን መላእክትና ከምድራውያን ቅዱሳን ጻድቃን ሁሉ በላይ ሆና ትከበራለች:: የቤተ ክርስቲያ ናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮም ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክ በመሆኗ መልዕልተ ፍጡራን (ከፍጡራን ሁሉ በላይ) መትሕተ ፈጣሪ (ከፈጣሪ በታች) ሆና ለድኅነታችን መሠረት እንደሆነች በሰፊው ያስረዳናል::

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ወልድ አምላካዊ የአድኅኖት ሥራ መሠረት መሆኗን በመግለጥ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም «ማርያም ድንግል ሙዳየ ዕፍረት ነቅዐ ፈልፈለ ማየ ሕይወት:: ፍሬ ከርሣ አድኃነ ኲሎ ዓለመ:: ወሠዓረ እምኔነ መርገመ:: ወገብረ ሰላመ ማዕከሌነ በመስቀሉ፤ ድንግል ማርያም ማየ ሕይወት የሚሆን ጌታ መገኛ ምንጭ ናት:: ፍሬ ማኅፀኗ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ሁሉ ከኃጢአትና ከፍዳ፣ ከመርገምና ከሞት አድኖአልና:: ከእኛም መርገመ ሥጋን፣

(160) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 110::*

(161) *መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 436:: ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 387:: «መልክአ ውዳሴ»፣ መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት፣* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 328::

መርገመ ነፍስን አጠፋልን፣ ደመሰሰልን:: በመካከል ሆኖም ሰውና እግዚአብሔርን በመስቀሉ አስታረቀ፣ ሰውና መላእክትን አገናኘ»(162) በማለት አስተምሮአል::

በአጭሩ ከላይ እንደገለጥነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም መሠረተ እምነት (ዶግማ) የእመቤ ታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት ልዩ ሥፍራ የሚሰጠው ከነገረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ረቂቅ ምሥጢርና ጥልቅ ግንኙነት ስላለው ነው::

## 3.2. የመጻሕፍተ ቅዳሴያት አስተምህሮ

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ዋና ማዕከል የሆነው የቅዳሴ ሥርዓት ስለ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ወላዲተ አምላክነት በስፋትና በጥልቀት ይመሰክራል:: የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ ዘወትር የሚያወሳና የሚገልጥ ሕያው ምሥጢር በመሆኑ መድኅነ ዓለም ክርስቶስን ወልዳ ያስገኘች የድንግል ማርያምን ሁለንተናዊ ዜና ሕይወት በመተንተን ያስረዳል::

ለምሳሌ ያህል ብንመለከት ከፍሬ ቅዳሴ በፊት የሚጸለየው የሥርዓተ ቅዳሴ ክፍል «ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት፤ ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ ዘይሠሪ ኃጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ:: ዝ ውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ፤ እሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ:: ቡሩክ የተባለ አሮን ከቤተ መቅደስ ይዞሽ የወጣ፤ ማዕከለ ሕያዋን ወሙታን ሆኖ እስራኤ ልን የታደገብሽ ማዕጠንተ ወርቅ፤ አንድም ቡሩክ እግዚአብሔር ለድኅነተ ዓለም መሣሪያ አድርጎ ማኅደረ እግዚአብሔር ከሚሆን ከአብርሃም ባሕርይ የመረጠሽ አንቺ ነሽ»(163) ይላል::

(162) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 156::
(163) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 70-71::



በዚህ ዓውደ ንባብ መሠረት ማዕጠንት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ ሲሆን፤ ወርቁ ደግሞ የንጽሕናዋና የቅድስናዋ ምሳሌ ነው:: ከዚህም ጋር ዕጣኑ የትስብእት፣ ፍሕሙ ደግሞ የመለኮት ምሳሌ ነው:: አንድም ፍሕም ከድንግል ማርያም ሰው የሆነው የሥግው ቃል የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ይኸውም ፍሕም የመዳሰስና ያለመዳሰስ ግብር እንዳለው ሁሉ፤ መዳሰስ የትስብእት፣ አለመዳሰስ ደግሞ የመለኮት ምሳሌ ነው:: (ዮሐ. 20÷27-29) ሌላው ምሥጢር ደግሞ ዕጣኑና ፍሕሙ በማዕጠንተ ወርቅ ውስጥ የተዋሐደበት የወርቅ ዘንግ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው:: ምክንያቱም በማኅፀነ ድንግል ማርያም መለኮትና ሥጋን ያዋሐደና አንድ ያደረገ እርሱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነውና:: ዳግመኛም ከድንግል ማርያም በተዋሐደው ሰው የሆነውና ራሱን የተወደደና ያማ ረ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ይህ ሥግው ቃል መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስን የሚደመስስ፤ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን የሚያድል ቡሩክ አምላክ ነው::(164)

ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤታችን ድንግል ማርያም እሳተ መለኮትን በማኅፀኗ የተሸከመች ማኅደረ መለኮት መሆኗን ሲገልጥ «ኃደ ረ ውስተ ከርሥኪ እሳተ መለኮት ዘአልቦቱ ጥዩቄ ወኢመጠን፤ መመርመር መወ ሰን የሌለበት ስፋሕ፣ ምሉዕና ረቂቅ የሆነ እሳተ መለኮት በማኅፀንሽ አደረ»(165) በማለት መስክሮአል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ታላቅና ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር አማካይነት ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ የቀደመውን የሰው ልጆችን አስከፊ ኑሮና አሰቃቂ ሁኔታ ቀይሯል:: ይህም ከላይ እንደገለጥነው የቤተ እሥራኤ ልን አስከፊ ገጽታ ቡሩክ አሮን ከቤተ መቅደስ በወሰዳት ማዕጠንተ ወርቅ ምክንያት እንደቀየረ ሁሉ፤ ወፍቁሬ ሰብአ የሆነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርም ከዘርአ አብርሃም ወገን ከሆነችው ከቅድስት ድንግል

(164) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 199-201::
(165) ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 129::

ማርያም በነሣው ሥጋና ነፍስ የእስራኤል ዘነፍስን ድኅነት ፈጽሟል::[166] (ገላ. 4÷4)

ይህንን ምሥጢር አስመልክቶ የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ሁለንተናዊ ክብር የሚያወሳው የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ክፍለ ንባብ "ዕፍረት ምዕዝት ይእቲ ማርያም:: እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሌዓል እምኩሉ ዕጣን:: መጽአ ወተሠገወ እምኔሃ:: ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሠምሩ እብ ወእሠርገዋ ይብተሬ ለማኅደረ ፍቁር ወልዱ[167]፤ እመቤታችን ድንግል ማርያም መዓዛ ድንግልናን፣ መዓዛ ንጽሕናንና መዓዛ ቅድስናን አስተ ባብራ ይዛ በመገኘቷ በዕፍረት (በሽቱ) ትመሰላለች:: የማኅፀኗ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም ከዕጣነ አሮን፣ ከዕጣነ ዘካርያስ የሚበልጥ ምዑዝ ባሕርይ ነው:: ከሰማያዊው ዓለም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ፈጽሞ ሰው ሆኖአልና:: ስለዚህም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና የምትሆን እመቤታችን ድንግል ማርያምን ለልጁ እናት ትሆነው ዘንድ መረጣት፣ ወደዳት፤ ማደሪያ እንድትሆ ነውም በንጽሕና፣ በቅድስና አስጌጣት ይላል::

በዚህ ገጸ ንባብ መሠረት ቅድስት ድንግል እመቤታችን በጣፋጭ ሽቱ (ዕጣን) መመሰሏ መዓዛ ቅድስናን፣ መዓዛ ንጽሕናንና መዓዛ ድንግልናን በሕይወቷ አስተባብራና አንድ አድርጋ ይዛ ስለተገኘች ነው:: ዳግመኛም በማኅፀነ ድንግል ማርያም ያደረውና በእርሷ ባሕርይ የተ ወለደው መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ከካህኑ አሮንና ከካህኑ ዘካርያስ ዕጣን የሚበልጥ አማናዊ መሥዋዕት በመሆኑ ምዑዝ ባሕርይ የሆነ አምላክ ነው:: ስለሆነም የምዑዝ ባሕርይ የክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና ያጌጠችና የተሸለመች በመሆኗ ለወልደ እግዚአብሔር እናትነት የበቃችበት ይህ ልዩ አምላካዊ ጸጋ

[166] McNamara ed., *Mother of the Redeemer: Aspects of Doctrine and Devotion*, 71. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 40.

[167] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 84::*



በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ድርሻ በግልጥ ያሳያል:: ምክንያቱም ወልደ አምላክ ወደዚህ ዓለም የመጣውና ከድንግል ማርያም የተወለደው ለቤዛ ዓለም፣ ለድኅነተ ዓለም ነውና::[168]

በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ከቅዱስ ወንጌል አዋጅ በፊት የሚደርሰው (የሚጸለየው) የእመቤታችን ምስጋና "ተፈሥሒ ኦ ዘንስእለኪ ዳኅና ቅድስተ ምልዕተ ክብር ድንግል በኵሉ ጊዜ ወላዲተ አምላክ እሙ ለክርስቶስ:: ...ተፈሥሒ ኦ ዘወለድኪ ለነ አማኑኤልሃ አምላክነ፤ ድኅነተ ሥጋን፣ ድኅነተ ነፍስን አሰጭን ብለን የምንለምንሽ ንጽሕት፣ ጽንዕት፣ ክብርት፣ ልዩ የምትሆኚ ክብርን የተመላሽ፤ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል የምትሆኚ አምላክን የወለድሽ የክርስቶስ እናቱ እመቤታችን ደስ ይበልሽ:: ... ፈጣሪያችን አማኑኤልን የወለድሽልን እመቤታችን ደስ ይበልሽ::»[169] በማለት እመቤታችን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር በስፋት ይመሰክራል::

ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ እንደገለጸው ከድንግል ማርያም የተወለደው አምላክ አማኑኤል መባሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የመሆኑን ምሥጢር ያስረዳናል:: በዚህም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሰማይና ምድርን ያገናኘች የሕይወትና የጽድቅ መሰላል መሆኗን ይገነዘቧል:: ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አማኑኤል የሚለውን ስያሜ አምላክ ወሰብእ ብለው ተርጉመውታል:: ከዚህ ምሥጢራዊ ትርጓሜም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ ዕርገተ ሥጋ በማኅፀነ ድንግል በመፈጸሙ በዚህ ረቂቅና ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር ሰው (ሥጋ) የባሕርይ አምላክ መሆኑን ይመለከቷል::[170]

[168] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 84::*

[169] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 81::*

[170] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 81::* ቅዱስ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ፣ *ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 421::*

ከላይ ከተመለከትናቸው የሥርዓተ ቅዳሴ ገጸ ንባባትና ትርጓሜ ምሥጢራት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያናችን ፍሬ ቅዳሴያትም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗንና በድኅነተ ዓለም ጉዞ ውስጥ ያላትን መሠረታዊ ድርሻ በስፋትና በጥልቀት ይመሰክራሉ፣ ያስተምራሉ:: ለአብነት ያህል ብንጠቅስ ቅዳሴ ሐዋርያትና ቅዳሴ እግዚእ የቅድስት ድንግል እመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት በመተባበር ሲመሰክሩ «ዘፈኖከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል፤ ተፀውረ በከርሥ ሥጋ ኮነ:: ወወልድከ ተዓውቀ እመንፈስ ቅዱስ፤ ልጅህን ከሰማይ ወደ ድንግል ማኅፀን የሰደድከው ሥጋም ሆነ መወለዱም በመንፈስ ቅዱስ ታወቀ»(171) በማለት ይገልጻሉ:: ከዚህ ዓውደ ንባብ ከሰ ማያት የወረደው፣ በድንግል ማርያም ማኅፀን ያደረውና በግብ ረ መንፈስ ቅዱስ የተወለደው መድኅን ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አለመሆኑን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::

ዳግመኛም የቅዳሴያቱ ገጸ ንባብ ሂድ፣ ውረድ፣ ተወለድ፣ ተሰ ቀል፣ ሙት ብለህ ወደዚህ ዓለም የላከው አንድያ ልጅህ በማኅፀነ ድንግል አድሮ ሥጋን ተዋሐደ፤ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ያለ አባት በመወለዱም የባሕርይ ልጅህ እንደሆነ ታወቀ በማለት የወልደ እግዚአብሔርን ሁለት ልደታት በምሥጢር ያስተ ረጉማል:: ይኸውም እግዚአብሔር ወልድ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከእመቤታችን ያለ አባት በመወለዱ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት መወለዱ ታውቋልና ነው:: ይህንን አስመልክቶ የቂሣርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ባስልዮስ ሲናገር «ወዓዲ ይደልወነ ንእመን ከመ ቦቱ ለወልደ እግዚአብሔር ፪ቱ ልደታት:: ቀዳሚ ልደቱ እምእግዚአብሔር አብ እምቅድመ ኵሉ መዋዕል:: ወዳግማዊ ልደቱ እምእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም በደኃሪ መዋዕል»(172) በማለት ገልጦ መስክሮአል:: (መዝ. 2÷7፤ 109÷3፤ ዮሐ. 16÷27-28፤ ገላ. 4÷4)

(171) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 118::

(172) ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ «በእንተ ምሥጢረ ሥጋዌ»፣ *ሃይማኖተ አበው፣* ገጽ 117::



የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም «ለእግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምን ዘንድ ይገባናል:: ይኸውም የመጀመሪያው ልደት ቅድመ ዓለም (ዓለም ሳይፈጠር፣ ዘመን ሳይቆጠር) ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ያለ እናት የተወለደው ልደት ነው:: ሁለተኛው ልደት ደግሞ በኋለኛው ዘመን (አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም) ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት የተወለደው ልደት ነው» ማለት ነው:: ከዚህም ኃይለ ንባብ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ግብር መወለዱ ከሦስቱ አካላት የተወላዲነት ግብር ያለው መሆኑን ያስረዳል፣ ያስገነዝባል:: ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም «እመሰ ኢእምኑ ልደቶ እምአብ እፎ የአምኑ ልደቶ እምድንግል»(173)፤ ወልደ እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ መወለዱን ካላመኑ ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱን እንደምን አድርገው ያምናሉ ሲል አስረግጦ ተናግሮአል::

ስለሆነም በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ብለን ከምናምንባቸው ከሦስቱ አካላት በተለየ አካሉ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከእመቤታችን ሰው የሆነው እርሱ እግዚአብሔር ወልድ ነው:: ምክንያቱም ከሦስቱ አካላት የተወላዲነት ግብር ያለው ወልደ እግዚአብሔር ብቻ ነውና:: ይኸውም አብ ወላዲ፣ አሥራፂ፤ ወልድ ተወላዲ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሠራፂ በሚለው የሥላሴ የግብር ሦስትነት ይታወቃል::

ይህንን አስመልክቶ ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እመቤታችንን ባመሰገነበት በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ «ከመዝ ነአምን ዘአልቦቱ እም በሰማያት፣ ወአብ በዲበ ምድር፤ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ለተወለደው ቀዳማዊ ልደቱ በሰማያት እናት እንደሌለው፣ ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም

(173) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"]* ፣ ገጽ 134-135::

ለተወለደው ደኃራዊ ልደትም በምድር አባት እንደሌለው እናምናለን፣ እንታመናለን፣ እናሳምናለን»(174) በማለት ገልጾ አስረድቷል::

ሌላው ደግሞ የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቅዳሴ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበብ እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ የተፈጸመውን የአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ወልድን ምሥጢረ ልደት ርቀትና ጥልቀት ሲያደንቅ «ወፈነውኮ ኀቤነ እንዘ ኢይትፈለጥ እምኀቤከ:: ነዮ ሀሎ ኀበ አንተ ሀሎከ፤ ነበረ ሰማያት ኀበ አቡሁ እንዘ ሀሎ ምድረ ምስለ ወላዲሁ፤ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅህ እግዚአብሔር ወልድ በምድር በምልዓት፣ በጌትነት ሳለ በሰማይም በምልዓት፣ በጌትነት ከባሕርይ አባቱ ከአንተ ጋራ አለ:: ዳግመኛም በምድር በማኅፀነ ማርያም ሳለ በሰማይም ከአንተ ጋራ በምልዓት፣ በጌትነት ይኖራል»(175) በማለት ተናግሮአል::

ዳግመኛም መጽሐፍ «ኮነንታሁ በአርያም ወኮነንታሁ በከርሠ ማርያም»(176) እንዳለው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በምልዓት፣ በጌትነት ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ሳይለይ በዘባነ ኪሩብ ሳለ፤ በምልዓት፣ በጌትነት በማኅፀነ ድንግል ማርያም አድሮአል:: ስለዚህም እመቤታችን ድንግል ማርያም ፈጣሬ ፍጥረታት የሆነውን ወልደ እግዚአብሔርን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ በመውለዷ እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፤ እመ እግዚአብሔር፣ ወላዲተ እግዚአብሔር ለመባል በቅታለች::

አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት በተወለደው ልደት ቀድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት

(174) ቅዱስ ያሬድ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 403::
(175) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 189::
(176) ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ [Emperor Zara Yacob ]፣ «*መጽሐፈ ብርሃን*» *["The Book of Light"]*፣ ed. C. Conti Rossini *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium* (Louvain: Secretariat de CorpusSCO, 1964), 62. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ «*መጽሐፈ ምሥጢር*» *[" The Book of Mystery"]*, ገጽ 2:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ «በእንተ ልደተ እግዚእ»፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 236:: *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 189::



የተወለደው ልደት በመታወቁና በመገለጡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ልደት የከበረ የባሕርይ አምላክ መሆኑን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::

ይህንን ምሥጢረ ተዋሕዶ አስመልክቶ ከላይ የጠቀስነው የቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ክፍለ ንባብ «... ኃደረ ውስተ ወለተ ሥጋ ዘይነብር መልዕልተ ኪሩቤል:: ለብሰ ሥጋ እሳት በላዒ:: ወተዓጽፈ አባለ መንፈስ ረቂቅ:: ተወልደ እምኀቤሃ ውስተ ከሡት:: ወኮነ ሕፃነ ዘይሥዕሎሙ ለሕፃናት በውስተ ማኅፀን:: ጠብለልዎ በአጽርቅት ለዘይትአጸፍ ብርሃነ፤ ጸወርት መንበሩ በሚሆኑ በኪሩቤል አድሮ የሚኖር አምላክ እርሱ በእመቤታችን ማኅፀን አደረ:: ፈታሒ በጽድቅ ጌታ (ረቂቅ መለኮት) ግዙፍ ሥጋን ተዋሐደ:: ቀድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከተወለደው ረቂቅ ልደት፤ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ በተዋሕዶ ነሥቶ ግዙፍ ልደትን ተወለደ:: ዳግመኛም ሕፃናትን አካለ ዘዮአክልን ሰጥቶ በማኅፀን የሚፈ ጥራቸው እርሱ በግእዘ ሕፃናት ተገለጠ:: ብርሃንን እንደ ልብስ ተጎናጽፎ የሚኖር ጌታን በጨርቅ ጠቀለሉት»(177) በማለት በአጽንኦተ ቃል ይመሰክራል::

በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ገባሬ ሠናዩ ካህን ሥጋ ወደሙን ለራሱ ተቀብሎ ከማቀበሉ በፊት «አአምን፣ አአምን፣ አአምን ወእትአመን፤ እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምእግዝእትነ ኩልነ ቅድስት ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወረሰዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ፤ በውስጥ በአፍአ፤ በነፍስ በሥጋ እስከ ዕለተ ሞት፣ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ አምናለሁ፣ እታመንማለሁ:: ንዕድ፣ ክብርት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውና ከባሕርየ መለኮቱ ጋር አዋሕዶ አንድ ያደረገው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ እንደሆነ በእውነት አምናለሁ፣ እታመንማለሁ»(178) በማለት ዘወትር ያውጃል::

(177) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 189:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 225-226::
(178) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 136-137::

በመሠረቱ የክርስትና ሕይወት ዋነኛ ዓላማ ከክርስቶስ ጋር ፍጹም መዋሐድና አንድ መሆን ነው። ይህ አንድነትና ኅብረት የሚመሠረተውና ፍጹም የሚጸናው ደግሞ ራሱ ባለቤቱ «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ» (ዮሐ. 6፥56) እንዳለው በቅዱስ ቁርባን አማካይነት ነው። በመሆኑም ፍሬ ድኅነት የሆነው ይህ ሰማያዊ ጸጋና ዘላለማዊ ክብር የሚገኘው በዚህ ታላቅና ቅዱስ ምሥጢር አማካይነት መሆኑ ከታወቀ፣ መብልዐ ጽድቅ ወስቴ ሕይወት የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ የነሣው መሆኑ ከታመነ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ የመሆኗ ምሥጢር ፈጽሞ አጠያያቂ አይሆንም።

ይህንን ጸጋ ክብር በተመለከተም የብሕንሳው ሊቅ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት ቅዳሴው "ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዓብየኪ። እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን፣ ወስቴ ሕይወት ዘበአማን፤ ድንግል ሆይ እንወድሻለን፣ እናከብርሻለን፣ እናገንሻለን። አንድም ድንግል ሆይ ክብርሽን፣ ገናንነትሽን እንናገራለን። ሥጋዊ ያይደለ መንፈሳዊ፣ አፍአዊ ያይደለ ውሳጣዊ፣ ምድራዊ ያይደለ ሰማያዊ የሚሆንና የዘለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ እውነተኛውን ምግብ፣ እውነተኛውን መጠጥ አስገኝተሽልናልና።"(179) ሲል ተናግሯል። ከዚህም ቃለ ውዳሴ በመብል ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ኃጢአትና መርገም የተሻረውና የተደመሰሰው ወልደ እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ደም በመሆኑ ቤዛዊተ በዓለም ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ሱታፌ በሚገባ መረዳትና መንዘብ ይቻላል።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እመቤታችን ድንግል ማርያምን መልዕልተ ፍጡራን (ከፍጡራን ሁሉ በላይ) መትሕተ ፈጣሪ (ከፈጣሪ በታች) አድርጋ የምታከብራትና የምታመሰግናት ከልዑል

(179) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 218። አባ ስብሐት ለአብ፣ "ነግሥ"፣ ገጽ 548፤



እግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣት ልዩ የአምላክ እናትነት ጸጋና ክብር መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። ዳግመኛም ምክንያተ ስሕተት ወሞት የሆነችው ቀዳሚት ሔዋን በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ የተከለከለውን የዕፀ በለስን ፍሬ ለራሷ በልታ ለአባታችን ለአዳም በመስጠቷ ምክንያት በሰው ልጆች ላይ ፍዳና መርገምን፣ ሞትና ጥፋትን አምጥታለች። በአንጻሩ ደግሞ ምክንያተ ድኅነት ወሕይወት የሆነችው ዳግሚት ሔዋን ቅድስት ድንግል ማርያም ዕፀ ሕይወት የሆነውን የማኅፀኗን ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሰጠችን የሰው ልጅ የዘላለም ሕይወትን አግኝቶባታል፣ አምላካዊ በረከትንም ተጎናጽፎባታል። ከላይ እንደገለጥነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያምን የመሠረተ እምነቷ ዐቢይ ክፍል አድርጋ የምታስተምረው የነገረ ድኅነት ምንጭና መሠረት ስለሆነ ነው።

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ ነገረ ማርያም የነገረ ድኅነት ምንጭና መሠረት ነው መባሉም አማናዊው መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው ከእመቤታችን በመሆኑ ነው። ስለሆነም ረቂቅና ድንቅ ለሆነው ለዚህ ታላቅ አምላካዊ የአድኅኖት ሥራ ብቸኛ መሣሪያ ሆና የተገኘችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በመሆኗ ስለ ክብሯና በነገረ ድኅነት ውስጥ ስላላት ልዩ ሥፍራ የሚናገረው ቅዳሴ የአምላክ እናትነቷን ምሥጢር ከዚህ በሚከተለው ቃለ ውዳሴ ያደንቃል።

> ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር ወንሕትታ ለቅድስት ድንግል በእንተ ጽንሳ ዘመንክር ለኵሉ። እንዘ ንብል ኦ ድንግል ዕቀበ ኅድረ ውስተ ከርሥኪ እሳት መለኮት ገጹ እሳት ልብሱ እሳት ከዳኑ እሳት እፎኑ ኢያውዓየኪ። ወጀቱ መንጦላዕት ዘነደ እሳት እደቲሁ ተደለወ። ወእደቲሁ ተንጦልዓ በውስተ ከርሥኪ። እምገቦኪ በየማንኑ። ወእምገቦኪ በጸጋምኑ። እንዘ ንስቲት አባል እንቲ። መንበር ኪሩባዊ ዘያንጸበርቅ ወዘየዓውደ ነደ እሳት እደቲሁ ተደለወ ወእደቲሁ ተተክለ በውስተ ከርሥኪ እንዘ ንዕስት መርዓት እንቲ። ኦ ከዊነ እም ዘምስለ እሙት። ጽበተ ከርሥ ዘምስለ

ርኅብ:: ጽንስ እንበለ ሩካቤ ከመ ንሕብ ዘእምቃለ ንባብ:: ሐሊብ ምስለ ድንግልና ጽሙር::[180]

የዚህ ቃለ ውዳሴና ቃለ አንክሮ ትርጓሜ ምሥጢርም ዳግመኛም የምሥጢራት ሁሉ ርእስ የሚሆን የምሥጢረ ሥጋዌን ምልዓትና ስፋት፣ ርቀትና ጥልቀት ወደ መናገር እንመለስ:: ዳግመኛም ንዕድ ክብርት የምትሆን ድንግልን ለሁሉ ዕፁብ ድንቅ የሚሆን የዕንሷን ነገር ድንግል ሆይ ሁለንተናዊ አካሉ እሳት፣ መጐናጸፊያውም እሳት የሚሆን ባሕርየ መለኮት በማኅፀንሽ ባደረ ጊዜ እንደምን አላቃጠለሽም? ብለን በአንክሮ እንጠይቃት፣ እንመርምራት:: ፍጹም የሆነ የእሳት መጋረጃስ በማኅፀንሽ ውስጥ ወዴት ተጋረደ? ወዴትስ ተዘጋጀ? በቀኝ ጎንሽ ነውን? ወይስ በግራ ጎንሽ ነውን? በሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት የተወሰንሽ ስትሆኚ ማለት እንደ ሌሎቹ ደቂቀ አዳም ሰካለ ዘየእክለን ገንዘብ ያደረግሽ ስትሆኚ ማኅደረ መለኮት፣ መንበረ መለኮት የመሆንሽ ምሥጢር ምን ይረቅ፣ ምንስ ይደንቅ!

ድንግል ሆይ የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ስትሆኚ ሁለንተናው በሚያቃጥል ነደ እሳት የተጋረደና የተከበበ፤ ጸወርተ መንበር የሚሆኑ ኪሩቤል የተሸከሙት የእሳት መንበር ወዴት ተዘረጋ? ከገረድነት ጋር ሳለ እናትነትሽ አንክሮ ይገባል፤ አንድም እናት ስትሆኚ ገረድ፣ ገረድ ስትሆኚ እናት ለሆንሽበት ለዚህ ምሥጢር አንክሮ ይገባል:: በዚህም ኃይለ ቃሉ ሊቁ ምሥጢረ ሥጋዌን “ርእሰ ምሥጢራት” ብሎታል::

ምክንያቱም የሥላሴ የአንድነት የሦስትነት ምሥጢር በጉላ በተረዳ የታወቀውና የተገለጠው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰው ከሆነ በኋላ ነውና:: መጽሐፍ «ወእሰቦ ዘእስመርመሩ ወኑኃ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት ድንግል፤ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት

(180) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 250-252::*



ድንግል ማርያም ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ልዩ ሦስት የሚሆኑ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን በጉላ በተረዳ ነገር ያወቃቸው የለም»[181] እንዲል::

አባ ሕርያቆስ በሥጋዌ ርስት ሲናገር እመቤታችን ወልደ እግዚአብሔርን በሥጋ ትወልደዋለችና እናት አላት፤ እርሱ ደግሞ በጥንተ ተፈጥሮ ይፈጥራታልና ገረድ አለ:: ዳግመኛም ከድንግልና ጋራ ሳለ እናትነት ወዮ አንክሮ ይገባል በማለት የምሥጢሩን ርቀትና ጥልቀት ያደንቃል:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም “ኦ ለዝንቱ መንክር ልዑል ሳዕለ ኵሉ ኅሊናት ... ድንግል ወለደቶ ለገባሬሃ ወለሊሁ ፈጠረ ወላዲቶ፤ ከኅሊናት ሁሉ ለራቀ፤ ለዚህ ድንቅ ምሥጢር አንክሮ ይገባል:: ... ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው፤ እርሱም እናቱን ፈጠረ»[182] ሲል እንደመሰከረ:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እናትነትን ስትታደል ድንግልናዋ ሳይሻር፣ ድንግልናን ስትታደል ደግሞ እናትነቷ ሳይለወጥ በመሆኑ ድንግል ወእም (ድንግልም እናትም) ናት:: ይኸውም ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ (ሰው የሆነ አምላክ) የመሆኑን ምሥጢር ያስረዳል:: በሌላ አገላለጽ ደግሞ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከእመቤታችን በተዋሕዶ ሰው በሆነ ጊዜ ባሕርየ መለኮቱ አለመለወጡ፤ እመቤታችን ጌታን በወለደችው ጊዜ ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡን በምሥጢር ያሳያል፣ ያስገነዝባል::

ከላይ የገለጥነው የቅዱስ አባ ሕርያቆስ ኃይለ ቃል ሰማይና ምድር የማይወስኑትንና የማይችሉትን ምሉዕ በኲለሄ የሆነውን አምላክ ከቀደመው ሰካለ ዘየአክለ ሳይለወጥ መወሰን፤ አንድም ከስፍሐት ከምልዓት ከርቀት ጋር ሳለ አለመለወጥ ወዮ አንክሮ ይገባል ሲል ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ለመለኮት ማደሪያነት የተመረጠችበትንና ለድኅነተ ዓለም መሣሪያነት የበቃችበትን ምሥጢር በማድነቅ ይገልጻል:: ዳግመኛም ንብ ከአውራው ድምፅ የተነሣ እንዲፀንስ እመቤታችንም

(181) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 163::*
(182) ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ “በእንተ ልደተ እግዚእ”፣ *ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 150::*

«ትፀንሲ» የሚለውን ቃለ መልአክ ሰምታ አካላዊ ቃልን እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ ለመፅነሷ፣ ወዮ አንክሮ ይገባል:: ከዚህም ጋር ሐሊብን (ወተትን) ከድንግልና ጋራ ደርቦ ለማስገኘት ወዮ አንክሮ ይገባል በማለት ያደንቃል:: እንደሚታወቀው በተፈጥሮ ሕግ ሥርዓት መሠረት ወተትን ማስገኘት የሚችሉት መዓስባት (ያገቡ ሴቶች) ብቻ ናቸው:: ደናግል ሴቶች ግን በድንግልናዊ ሕይወት ሳሉ ወተትን ፈጽሞ ሊያስገኙ አይችሉም::

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ግን «አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» (ሉቃ. 1÷28፣ 42) ተብሎ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤልና በቅድስት ኤልሳቤጥ አንደበት የተመሰከረላት ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር በመሆኗ ይህ ልዩ ጸጋና ክብር ማለትም በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልና ተሰጥቷታል:: ይህንን አስመልክቶ መጽሐፍ ሲናገር «የዓጽብ ንቅዓተ ሐሊብ እምእጥባተ ድንግል እንተ ኢተአምረ ብእሴ:: ወኢይትከሃሎን ለአንስት አውግዞ ሐሊብ ዘእንበለ ይትራከባ ምስለ ዕደው» ይላል:: ይህም ማለት «ወንድ ከማታውቅ ከድንግል ጡቶች ወተት መገኘት ምን ይደንቅ? ምክንያቱም ለዚህ ዓለም ሴቶች ከወንዶች ጋር ሳይገናኙ ወተትን ማስገኘት አይቻላቸውምና ነው::»[183]

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ልዩ የሆነ ሥፍራ የሚሰጣት ከደቂቀ አዳም የተለየ ሰብአዊ ባሕርይ ስላላት አይደለም:: ይኸውም ከላይ በተጠቀሰው የቅዳሴ ማርያም ዓውደ ንባብ ላይ እንዳየነው «እንዘ ንስቲት እባል እንተ» የሚለው ኃይለ ቃል ቅድስት ድንግል እመቤታችን በሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት የተወሰነች የደቂቀ አዳም ወገን መሆኗን በግልጥ ያስረዳል:: ስለሆነም ምንም እንኳን እመቤታችን በሰብአዊ ተፈጥሮዋና ባሕርይዋ ከደቂቀ አዳም ወገን ብትሆንም ቅሉ መዓርገ ክብሯና ልዕልናዋ ግን ከልዑለ ባሕርይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣት ልዩ ጸጋና በረከት በመሆኑ መልዕልተ ፍጡራን እንደሆነች ልብ ይሏል::

(183) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 251-252::



ሌላው አስደናቂ ምሥጢር ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እናትነትን ከገረድነት ጋር አስተባብራ ይዛ የመገኘቷ ምሥጢር ነው:: ይህም በሌላ አገላለጽ ሲነገር ድንግል ማርያም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን በሥጋ ስለወለደችው እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ትባላለች፤ እንዲሁም ደግሞ እርሷ በሥጋ የወለደችው መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፣ ወልደ አምላክ በመሆኑ አመተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ገረድ ወይም አገልጋይ) ተብላለች:: እመቤታችንም ይህንን አማናዊ ምሥጢር በመግለጥ ለመልአከ ብሥራቷ ለቅዱስ ገብርኤል «ነየ አመተ እግዚአብሔር፣ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ እነሆኝ የእግዚአብሔር ገረዱ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ» (ሉቃ. 1÷38) ብላ መስክራለች:: ከዚህም ጋር እግዚእ ስብሐት ለሆነው አምላክ ምስጋናን ባቀረበችበት ጸሎቷም «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች::» (ሉቃ. 1÷46-48) ስትል በፍጹም ትሕትና በአጽንኦት ተናግራለች::

ከላይ የተመለከትነው የቅዳሴ ማርያም ቃለ አንክሮ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አካላዊ ቃል ረቂቅና ድንቅ በተሰኘው የሥጋዌ ምሥጢር ከእርሷ ሰው በሆነ ጊዜ አለመለወጧን በግልጥ ያስረዳል፣ ያስገነዝባልም:: በዚህም ቅድስት ድንግል እመቤታችን ሰማይና ምድር የማይወስኑትንና ሊሸከሙት የማይቻላቸውን ኃያል አምላክ በማኅፀኗ መወሰኗ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን የእናትነት ክብርና ጸጋ ከሌሎች ፍጡራን ሁሉ ልዩ ያደርገዋል::

ይህንን አማናዊ ምሥጢር አስመልክቶም ሌላኛው የቅዳሴ ክፍለ ንባብ «እግዚአብሔር አብ ዘፈነወ ወልዶ ዋሕዶ:: ከመ የኀድር ውስተ ሥጋ ወለተ እንተ ኢተአምረ ምተ:: ሠዓሊ ሕፃናት እንዘ ኢይትጋባእ:: ተሰብአ እንዘ አምላክ ውእቱ:: ወተወልደ እንዘ እሳተ መለኮት ውእቱ[184]፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አብ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጁን ሂድ፣ ውረድ፣ ተወለድ ብሎ ወደዚህ ዓለም ላከው:: ዘርዐ ብእሲን በማታውቅ፤ ንጽሕት

(184) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 294:: Brock, *Bride of Light*, 38, 119.

በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በሰዕልና በሆነችው በእመቤታችን በድንግል ማርያም ማኅፀን ያድር ዘንድ:: ዳግመኛም ሕፃናትን በማኅፀን የሚፈጥር እርሱ ሳይወሰን በምልዓት፣ በጌትነት በማኅፀን አደረ:: አምላክ እንደመሆኑም መጠን ሳይወሰን ሰው ሆነ፤ ባሕርየ መለኮቱ ሳይለወጥ ከድንግል ማርያም ተወለደ በማለት የምሥጢሩን አድማስ አምልቶና አስፍቶ ይናገራል::

በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚጸለየውና በጉባኤ ኒቅያና በጉባኤ ቁስጥንጥንያ የተረቀቀው ጸሎተ ሃይማኖት [Niceo-Constantinopolitan Creed] የእመቤታችን የድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢር አጉልቶ ያሳያል:: ይኸው የሃይማኖት ጸሎት "... ዘበእንቲአነ ሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ...፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ዘኮነ በከመ ትቤሉ ከማለቷ የተነሣ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን፣ ነሥቶ ሰው ሆነ"[185] በማለት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በምሥጢረ ተዋሕዶ አማካይነት ለተፈጸመው አምላካዊ የማዳን ሥራ መሠረት መሆኗን አስረግጦ ይመሰክራል:: በዚህም የምሥጢረ ሥጋዌ ዋነኛውና ተቀዳሚ ዓላማ ድኅነተ ዓለም በመሆኑ ይህ አምላካዊ የማዳን ሥራ አማናዊ እንዲሆን በማድረግ በኩል የእመቤታችን የድንግል ማርያም አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ይገነዘቧል::

ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በወላዲተ አምላክ በድንግል ማርያም መሠረትነት ወልደ እግዚአብሔር በፍጹም ትሕትና ራሱን ለዓለም መግለጡን አስመልክቶ ሲናገር:- "መንክርኬ ወዕፁብ ወመድምም ዝንቱ ነገር:: ምንትኑ አሐቢ ወእነክር:: ሀልዎተኩ ምስለ አቡከ በአርያም ወበቅድስና፤ ወሚመ ከመ ሕፃን ውስተ ሕፅነ እምከ፤ አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ የሆነበት ይህ ምሥጢረ ተዋሕዶ በእውነት ዕፁብ ድንቅ ነው::

(185) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 274::*



ማናቸውን አስቤ ላድንቅ? በመለኮታዊ ባሕርይህ ባለመመርመር ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ተብለሕ በመመስገን ከባሕርይ አባትህ ከአብ ጋራ በቅድምና መኖርህን ላድንቅን? ወይስ በአምሳለ ሕፃን ተገልጠህ በግእዘ ሕፃናት ሆነህ በእናትህ እቅፍ መያዝህን?"[186] እያለ የተዋሕዶ መሠረት፣ የድኅነተ ዓለም ምክንያት በሆነችው በእመቤታችን በድንግል ማርያም ሕይወት ኃያሉ አምላክ የፈጸመውን ታላቅ የቸርነት ሥራ በአንክሮ አውስቷል::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የቂሣርያው ሊቅ ቅዱስ ባስልዮስ በቅዳሴው መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሰው የሆነበትን ዋና ዓላማ ሲያስረዳ:-

> ወሶበ አበስነ ወዓለውነ ትእዛዘከ በአስሕቶ ከይሲ ርኅቅነ እምሕይወት ዘለዓለም:: ወወፃእነ እምገነተ ትፍሥሕት:: አንተሰ ኢገደፍከነ ለዝሉፉ:: አላ ሐወጽከነ በነቢያቲከ ቅዱሳን:: ወበደኃሪ መዋዕል አስተርአይከ ለነ ለእለ ንነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት:: ወእብሬህከ ላዕሌነ ብርሃነ ዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል:: ተሠገወ ወኮነ ሰብአ፤ ወመሐ ረነ ፍኖተ ሕይወት:: ወረሰየነ ሎቱ ሕዝበ ንጹሐ::[187] ሲል

በአጽንኦት ገልጾአል::

የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም አቤቱ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ምክረ ከይሲን ሰምተን ትእዛዝህን ባፈረስንና በበደልን ጊዜ ከዓቂበ ሕግ በመውጣታችን ምክንያት ከዘላለም ሕይወት ተለየን፤ ተድላ ደስታ ከሚደረግባት ገነትም ወጣን:: ርኅቀ መዓት ወብዙኅ ምሕረት የሆንክ አንተ ግን እንደ ገቡ ይውጡ፣ እንደ ወጡም ይቅሩ አላልኸንም:: ይልቁንም በዐበይት ነቢያት፣ በደቂቀ ነቢያት አድረህ በተስፋ ትንቢት ጎበኘኸን እንጂ::

(186) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 329::*
(187) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 340-341::*

ዳግመኛም የተነገረው ትንቢት ሲፈጸም፣ የተቆጠረው ሱባኤም ሲደርስ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ በልጅህ ህልው ሆነህ በጨለማ ኃጢአትና በሞት ጥላ ሥር ለነበርን ለእኛ ተገለጽክልን:: ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን የጌታችን የፈጣሪያችን የልጅህ የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃነ ረድኤት በላያችን ላይ አበራህ:: በማይመረመርና ረቂቅ በሆነ የመንፈስ ቅዱስ ግብርም ወላዲተ አምላክ "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ" ከማለቷ የተነሣም ሰው ሆነ:: ከኃጢአት ብቻ በቀር የእኛን ባሕርይ ከእርሷ ባሕርይ ነሥቶ ፍጹም ሰው ሆነ፤ ሃይማኖተ ወንጌልን፣ ምግባረ ወንጌልንም አስተማረን፤ እግረ ልቡናችንንም ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት መርቶ አደረሰን:: ለርስቱ የተለየ ወገንና ለመንግሥቱም የተመረጠ ትውልድ አደረገን ማለት ነው::

ከዚህ በተጨማሪም ይኸው ሊቅ "... ወመጠወ ርእሶ በፈቃዱ ከመ ያንግፈነ እሞት እንተ ነግሠ ላዕሌነ:: ዝንቱ ውእቱ ዘተእኅዝነ በምክንያቱ:: ወቀነየነ በኃጢአትነ:: ወወረደ ውስተ ሲኦል እምዲበ መስቀል፤[188] ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በፍዳና በመርገም ተይዘን በነበርን በእኛ ላይ ሰልጥኖብን ከነበረ ከጥንተ ጠላታችን ከዲያብሎስ እጅ ያድነን ዘንድ በፈቃዱ ወደ ራሱን ለሕማም፣ ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና:: በኃጢአታችንና በበደላችን ምክንያት ሞት ስለገዛን ማኅየዊ የሚሆን ጌታ በዕለተ ዓርብ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለይቶ ከመልዕልተ መስቀል በአካለ ሥጋ ወደ ታሕተ መቃብር ወረደ:: በአካለ ነፍስም ወደ ሲኦል ወርዶ "እለ ውስተ ሲኦል ፃኡ፤ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ፤ በሲኦል ግዞት ያላችሁ ወደ ነጻነት ገነት ውጡ፤ በድቅድቅ ጨለማ ኃጢአት ውስጥ የተቀጣችሁም ወደ ብርሃን ጽድቅ ተገለጡ" ብሎ ነፍሳትን አወጣ በማለት መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ነፍስ የፈጸመውን የቤዛነት ሥራ አስረግጠ ተናግሮአል:: ቅዱስ ባስልዮስ በዚህ የምሥጢረ ድኅነት ዓለም አስተምህሮው ወላዲተ

[188] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 341-342::



አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻና መሠረታዊ ሚና በጉልህ አስረድቷል::

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ የድኅነተ ዓለም ሥራ የተከተናወነው በድንግል ማርያም ምክንያተ ድኅነትነትና መሣሪያነት በተፈጸመው የሥጋዌ ምሥጢር መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህም ማለት አካላዊ ቃል ከእመቤታችን በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሆነ ሲባል ሥጋንና ነፍስን ደመ ነፍስንም ነሣ ማለት መሆኑን ፈጽሞ ማመን፣ ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት ያስፈልጋል:: ይህ ካልሆነ ግን ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን ብቻ እንጂ ነፍስን አልነሣም፣ አልተዋሐደም ወደሚለውና በሁለተኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሆነው በጉባኤ ቁስጥንጥንያ ተወግዞ ወደተለየው አቡሊናርዮሳዊ የኑፋቄ ትምህርት [Apollinarianism /Apollinarian Heresy] ይወስዳል::

ይህ የአቡሊናርዮስ [Apollinarius (A.D. 310-390)] የኑፋቄ ትምህርትም በአጭሩ ሲገለጥ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በኋለኛው ዘመን ለድኅነተ ዓለም ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ "ህየንተ ነፍስ ወልቡና ኮነ መለኮቱ፤ አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ ስለ ሕያዊት ነፍስ ፋንታ መለኮቱ ሕይወትና ዕውቀት ሆነው"[189] የሚል ነው:: ይህ ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሊቃውንት አበው ድርሳናት በስፋትና በጥልቀት የተገለጸውን የነገረ ድኅነት ምሥጢር ያፋልሳል፣ ይንዳልም::

ይኸውም አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን ብቻ እንጂ ነፍስን አልነሣም ማለት ድኅነትን ይሻ የነበረው የሰው ልጅ በሥጋው ብቻ እንጂ በነፍሱ አልዳነም ማለት ነው:: ዳግመኛም ወልደ እግዚአብሔርን በሥጋዌ ርስት፣ በሥጋዌ ሥርዓት ሞተ ስንል የነፍስንና የሥጋን መለያየት እንጂ ሞት የማይገባው መለኮትን

[189] አባ ጎርጎርዮስ፤ *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤* ገጽ 136-140:: Kelly, *Early Christian Doctrines*, 289-295.

ማለታችን አይደለም። ምክንያቱም መድኅነ ዓለም ክርስቶስ በተዋሕዶ ያልነሣውንና ያልተዋሐደውን ሊያድነውና ካሣ ሊከፍልለት አይችልምና ነው። ይህንን አስመልክቶ በዘመኑ የነበረው ወርቃማው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ሲመልስ "ኢያድኅኖ ለዘኢነሥኦ" ["What has not been assumed has not been saved; and what has been saved has been assumed."](190) በማለት ተናግሮአል። ይህም ማለት ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ ያልነሣውንና ያልተዋሐደውን አላዳነውም፤ ካሣም አልከፈለለትም ማለት ነው።

መጻሕፍት አምላካውያት በስፋት እንደሚነግሩን ግን የሰው ልጅ ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፉና ትእዛዘ እግዚአብሔርን በማፍረሱ ፈጣሪው እግዚአብሔርን በሥጋውም በነፍሱም አንድ ሆኖ ተካክሎ በድሏል። በዚህም ምክንያት በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፤ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተፈርዶበታል። በነገረ ድኅነት ትምህርት [Soteriology] ደግሞ በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት በፍዳና በመርገም ተይዞ የነበረውን የሰውን ልጅ ለማዳን የሚመጣው አዳኝ የበዳዩን (የካሣ ፈላጊውን) ባሕርይ ፈጽሞ ባሕርይው ማድረጉ በእጅጉ አስፈላጊና የግድም ነው። ስለዚህም መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፤ ከነፍሷ ነፍስን በተዋሕዶ መንሣቱ የሥጋዊውን አማናዊነትና የሰው ልጆችን ፍጹም ድኅነት ያስገነዝባል።

ሊቁ ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በምሥጢረ ሥጋዌ በኩል ስለተፈጸመው የድኅነተ ዓለም ምሥጢር ሲናገር "አማኑኤል ሞተ ከመ ሞተ ዚአነ። ዘውእቱ ተፈልጦተ ነፍስ እምሥጋ፤ አማኑኤል አምላካችን፤ አማኑኤል መድኃኒታችን እንደ እኛ ያለ ሞትን በእውነት ሞተ። ይኸውም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው።"(191) ሲል በአጽንኦተ ቃል መስክሮአል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ መስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፤ ክቡር ደሙን አፍስሶ፤ ቅድስት ነፍሱን ቤዛ አድርጎ ክሶ፤ በገዛ ሥልጣኑ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በፈቃዱ ለየ። በዚህን ጊዜም በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ወርዶ ሙስና መቃብርን ሻረልን፤ ደመሰሰልን፤ በአካለ ነፍስ ደግሞ ወደ ሲኦል ወርዶ በዲያብሎስ ግዞትና ቁራኝነት ተይዘው ለነበሩ ነፍሳት ሰላምንና የምሥራችን ሰበከላቸው፤ ግእዛንንም ሰጣቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን መለኮት ከሥጋም ሆነ ከነፍስ ለዓይን ጥቅሻ (ለቅጽበተ ዓይን) ያህል እንኳን አልተለየም። ከዚህ አምላካዊ የምሥጢረ ድኅነት ጉዞም ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን መሠረታዊና ወሳኝ ሱታፌ ልብ ይሏል።

ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በቅዳሴው ሲናገር "ለብሰ ሥጋ ዘይማስን። ወረሰዮ ዘኢይማስን። ወበይእቲ ሥጋ ተቀሥፈ ዘኢይትቀሠፍ አምላክ"(192)፤ የሚያልፍ፤ የሚጠፋ ሥጋን ተዋሐደ፤ የማያልፍ፤ የማይጠፋም አደረገው። ዳግመኛም በተዋሕዶ ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋም የማይገረፈው ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ተገረፈ በማለት ገልጾአል። በመሆኑም በነገረ ድኅነት ትምህርት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ለመሆኑ መሠረታዊ ማስረጃና ምስክር ነው። ይህ ደግሞ ለሰው ልጆች መዳን ማረጋገጫ ዋስትና ከመሆኑም ሌላ የመለኮታዊ ክብር ተካፋይ መሆናችንንም ያስገነዝባል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ ሲያስረዳ "ኦ ዘአፍቀርከ ትሕትናሁ ለእጓለ እመሕያው እምዕበዮሙ ለመላእክት። ኦ ዘአፍቀርከ ንዴተ ዚአሁ ለአዳም

(190) St. Gregory of Nazianzus, *On God and Christ: The Five Theological Orations and Two Letters to Cledonius*, trans. Frederick Williams and Lionel Wickham (Crestwood, N. Y.: St. Vladimir's Seminary Press, 2002), 156-164. አባ ጎርጎርዮስ፤ *የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ*፤ ገጽ 136-142። Kelly, *Early Christian Doctrines*, 295-302.

(191) ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፤ "በእንተ ትሥጉተ እግዚእ"፤ *ሃይማኖተ አበው*፤ ገጽ 367-368።

(192) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፤ ገጽ 360።

እመዛግብቲሆሙ ለነገደ አብርሃም፤ ልዑላን ከሚሆኑ ከሰማያውያን መላእክት ባሕርይ ይልቅ ከትሑታን ወገን የሚሆን የአዳምን ሥጋ ለመዋሐድ የመረጥህ፤ ዳግመኛም አብርሃም እንግድነት ከተቀበላቸው ከመላእክት ባሕርይ ይልቅ የአዳምን ባሕርይ የወደድህ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ...»[193] ሲል በምሥጢር ሠረገላ እየተሳበ አምላካዊ የድኅነተ ዓለም ሥራ የተከናወነበትን የሥጋዌን ጥበብ ያደንቃል:: (ዕብ. 2÷16፤ 13÷2)

ከዚህም ሌላ ደግሞ ሃይማኖታቸው የጸና፣ ምግባራቸው የቀና፤ በጉባኤ ኒቅያ ወልድ ዋሕድ የምትል ኦርቶዶክሳዊ እምነትን የሰበኩ ሠለስቱ ምእት (ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ሊቃውንት አበው) ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በሐዲስ ተፈጥሮ የሰው ልጆችን ያዳነበትና ያከበረበት የድኅነተ ዓለም ምሥጢር ከወላዲተ አምላክ ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋ የተፈጸመ መሆኑን በመግለጥ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

> ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል እንቲአነ ሥጋ:: እኮ እምሰማያት ዘአውረድከ፤ ሕማማተ መስቀልን ተቀብሎ ማኅየዊ በሚሆን ሞቱ ቤዛ ሆኖ ከኃጢአትና ከፍዳ ዓለምን (የሰው ልጆችን) ያዳነው ሥጋ ንዕድ ክብርት ከምትሆን ከእመቤታችን የነሣኸው የእኛ ሥጋ እንደሆነ እንጂ ከሰማይ ያወረድኸው እንዳይደለ አስበህ አድነን::
>
> ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘግሕታተ መዋቅሕት ዘፆረ፤ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣኸው ሥጋ ጽኑ መከራ መስቀልን፤ አንድም ግርፋትን፣ ቅንዋትን የተቀበለው እኛን ለማዳን እንደሆነ አስበህ አድነን::
>
> ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘሐመ ወሞተ፤ ከእመቤታችን የነሣኸው ሥጋ መከራን የተቀበለውና የሞተው እኛን ለማዳን እንደሆነ አስበህ አድነን::
>
> ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት፤ ከቅድስት ድንግል እመቤታችን የነሣኸው ሥጋ በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው እኛን ለማዳን፤ አንድም በኲረ ትንሣኤ ሆነህ እኛን ለማስነሣት እንደሆነ አስበህ አድነን::
>
> ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘዓርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ፤ ንዕድ፣ ክብርት ከምትሆን ከእመቤታችን የነሣኸው ሥጋ በሰማይ ደመና፣ በመላእክት ምስጋና፣ በብርሃን፣ በቅዳሴ፣ በሥልጣን ያረገው በኲረ ዕርገት ሆነህ እኛን ለማሳረግ እንደሆነ፤ አንድም በአባቱ ዕሪና በክብር፣ በጌትነት፣ በምልዓት የተቀመጠው እኛን ለማዳን እንደሆነ አስበህ አድነን::
>
> ወካዕበ ይመጽእ በውእቱ ሥጋ ምስለ ኃይለ መስኮቱ እግዚአብሔር አምላክነ፤ ዳግመኛም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ዓለምን ከማሳለፍ ጋራ በዚህ ሥጋ ማለት ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ዳግመኛ ይመጣል::[194]

ከዚህም ጋር ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የእግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ሰው የመሆን ዋና ዓላማ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን መሠረታዊ ትሥሥር ሲናገር፡- «ወእምዝ ሶበ ርእየ ከመ ኢበቍዓ ለአድኅኖተ ዓለመ ደመ ነቢያት ቅዱሳን እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ፤ ፈነወ ለነ ወልዶ ወድኅነ ወመቤዝወ ከመ ይባልሖ ወይቤዙ»[195]፤

[193] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 376::



[194] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 301-302::

[195] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 389::

ለነቢያት ሞት መጀመሪያቸው ከሆነው ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ መጨረሻው ካህነ ብሉይ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለሙን ለማዳን እንዳልበቃ፣ እንዳልረባና እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ ፈጽሞ ያድነን ዘንድ ቤዛ መድኃኒት የሚሆን ልጁን ላከልን በማለት መስክሮአል:: ይህ ኃይለ ቃል በፍዳና በመርገም የወደቀውን ዓለም ማዳን የሚችል ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አንዳችም ኃይል እንደሌለ ያስገነዝበናል:: ስለዚህም ከቅድስት ድንግል ማርያም በኤፍራታ ቤተ ልሔም የተወለደው መድኅን አምላክ፣ ወልደ አምላክ መሆኑ ከታወቀና ከተረዳ የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት ለነገረ ድኅነት ትምህርት መሠረትና ምንጭ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል::

ዳግመኛም ይኸው አባት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ድኅነተ ዓለምን የፈጸመበትን ረቂቅና ድንቅ አምላካዊ ጥበብ አስመልክቶ ሲገልጥ:- «ጥበብሰ መድኃኒነ ውእቱ ዘቤዘወነ በጥብሐ ሥጋሁ ወተሳየጠነ በንዝሐተ ደሙ:: ወኃረየነ ለመንግሥቱ ለዓለመ ዓለም»(196) ብሏል:: ትርጓሜ ምሥጢሩም ጥበብ የተባለው ኅብስተ ሕይወት የሚሆን ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ያዳነን፣ ማየ ሕይወት የሆነውን ክቡር ደሙን አፍስሶ የዋጀን፤ የማታልፍና የማትለወጥ ርስቱንም ለመውረስ የመረጠንና ያበቃን እርሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው::

የቂሣርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ባስልዮስ በሊጦን ጸሎቱ ይህንን ምሥጢር ሲያብራራ «ቀዳሚ ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ፤ እስመ አንተ ውእቱ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያስተተ ኃጢአተ ዓለም ተሣሃለነ:: እስመ ወፈድከ እምሰማይ በመስፈርተ ጥበቡ ለአቡከ፤ ከመ ታድኅን ለሕኮተከ ዘአንተ ሰሐኮ ወሞቱ ዘይሜምአን፤ ለባሕርይ አባቱ ለእግዚአብሔር አብ ኃይሉ፣ ጥበቡ፣ ምክሩ፣ መገለጫውና መታወቂያው የሚሆን የባሕርይ ክብሩን በጸጋ የሚሰጥ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የዓለሙን ኃጢአት የምታስወግድ፣ የሰው ልጆችን በደል የምታስተሠርይ፤ አንድም መርገመ ሥጋ፣

(196) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 395::



መርገመ ነፍስን የምታጠፋ የእግዚአብሔር አማናዊ መሥዋዕቱ አንተ ነህና ይቅር በለን፣ እዘንልን፣ ራራልን:: ረቂቅና ጥልቅ በሆነው በባሕርይ አባትህ ጥበብ ከሰማይ ወርደሃልና ማለት ከልዕልና ወደ ትሕትና መጥተህ ሰው ሆነሃልና:: ይኸውም የሚለወጥ መዋቲ የሚሆን አንተ የፈጠርኸው አዳምን (የሰው ልጆችን) ታድን ዘንድ ነው»(197) በማለት አስገንዝቧል::

የሰባክያን አክሊል፣ የአትሮንስ ንጉሥ በመባል የሚታወቀው ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን አባት ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ለድኅነተ ዓለም ሲል በወላዲተ በአምላክ በድንግል ማርያም በኩል የፈጸመውን ረቂቅ የሥጋዌ ምሥጢር ሲያደንቅ:- «ኃደረ ውስተ ወለተ ሥጋ እንዘ ኢየኅርቅ እመንበረ:: ተፀንሰ በከርሥ እንዘ ኢይትጋባእ እምኵለሄ ምልዓቱ:: ተዓቍረ ውስተ ማኅፀን እንዘ ኢየሐፅፅ በሳዕሉ፤ ወተወልደ እንዘ ኢይትዌሰክ በታሕቱ»(198) በማለት ተናግሮአል::

የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከሥልጣኑ፣ ከምልዓቱ፣ ከጌትነቱ፣ ከዙፋኑ ሳይለይ በእመቤታችን በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ:: በባሕርዩ፣ በአካሉ፣ በጌትነቱ ከምልዓቱና ከስፋቱ ሳይወሰን ተፀነሰ:: ከሦስትነቱ ጎድሎ ወደ ሁለትነት ሳይሔድ በማኅፀነ ድንግል አደረ:: ሥጋን መዋሐዱን ምክንያት አድርጎ አራተኛ ሳይጨመርበት ከድንግል ተወለደ:: ዳግመኛም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በአምላክነቱ ሕፀፀ ክብር፣ ሕፀፀ አካል ሳይኖርበት በማኅፀን አደረ፤ ዳግመኛም ሥጋ ምልዓተ ክብር፣ ምልዓተ አካል ሳይሆነው ተወለደ:: በዚህም የሥጋዌ ልደት ምክንያት በአንድነቱ ምንታዌን (ሁለትነትን)፤ በሦስትነቱ ደግሞ ርባዔን (አራትነትን) አላመጣም ማለት ነው::

ቀደም ብለን በተደጋጋሚ እንደገለጽነው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ድኅነት አስተምህሮ መሠረት በወልደ እግዚአብሔር

(197) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 61-62::
(198) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 403::

ሰው መሆን የተፈጸመው የድኅነተ ዓለም ሥራ ሐዲስ ተፈጥሮ መሆኑን ተመልክተናል። ስለሆነም ለዚህ አምላካዊ የአድኅኖት ሥራ ሰውን በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በመልኩ አክብሮ የፈጠረው የልዑል ባሕርይ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣት በእጅጉ አስፈላጊና የግድም ነው። ይህንን አምላካዊ የቸርነት ሥራ አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲናገር፡-

> ኦ ኂሩት ዘመጠነዝ ኂሩት። ኦ ፍቅር ዘመጠነዝ አፍቅሮተ ሰብእ። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ አምላክ እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት። ... ኦ እእዳው እለ ለሐኳሉ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል። ኦ እእጋር እለ እንሶስዋ ውስተ ገነት ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል። ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈሰ ሕይወት ብሂዓ መጸጸ ዘምስለ ሐሞት ሰረበ።(199)

ይህን ያህል ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው! ወዮ ለዚህ አንክሮ ይገባል። ይህን ያህል ሰውን መውደድስ እንደምን ያለ ፍቅር ነው! ወዮ ለዚህ አንክሮ ይገባል። ፍቅረ ደቂቀ እጓለ እመሕያው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁን ከልዑል ዙፋኑ ስቦ ወደዚህ ዓለም አወረደው፤ እስከ መስቀል ሞትም አደረሰው። ... አዳምን የፈጠሩ እጆች በቀኖት ተቸነከሩ ወዮ! አዳም ሆይ ወዴት ነህ? እያሉ በገነት የተመላለሱ እግሮች በቀኖት ተቸነከሩ ወዮ! በአዳም ሕይወት ልጅነትን በንፍሐት ያሳደረ አፍ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ መጻጻን ጠጣ ወዮ! እያለ ያደንቃል።

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት የመሠረተ እምነቷ መድበልና የምሥጢረ ሃይማኖቷ መዝገብ ናቸው። ስለሆነም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በድቀተ ኃጢአት ውስጥ ለነበረው ዓለም የሰጠውን አስደናቂ የፍቅር መልስ የሚያሳዩ፤ እንዲሁም የመድኅነ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላካዊ የማዳን ሥራ የሚመሰክሩና ወሰን፣ ድንበር የሌለውን አባታዊ ፍቅሩንና

(199) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 406-407።





**ሥዕል 6:- የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት**

"ኦ ኂሩት ዘመጠነዝ ኂሩት። ኦ ፍቅር ዘመጠነዝ አፍቅሮተ ሰብእ።"

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 359)

"በፈቃዱ ለሕማም ተሰጠ። ሕሙማንን ያድን ዘንድ ታመመ። የተፍገመገሙትንም ያጸናቸው ዘንድ። የተጣሉትን ያገኝ ዘንድ የሞቱትንም ያድን ዘንድ። ሞትንም ይሽር ዘንድ የሰይጣንንም ማሠሪያ ይቈርጥ ዘንድ። ... ሲዖልንም ይረግጥ ዘንድ የሕይወትንም ደጅ ይከፍት ዘንድ።"

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 148)

ቸርነቱን በአድናቆት የሚገልጹም ናቸው፡፡ ስለሆነም በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ድኅነት አስተምህሮ መሠረት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማሙና ስቅለቱ፣ ሞቱና ትንሣኤው በኃጢአት የወደቀውንና በበደል የረከሰውን፤ ንጽሐ ጠባይዕ ያደፈበትንና ቅድስና ባሕርይ የጎሰቆለበትን የሰውን ልጅ ሕይወት ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ ለማደስና ለመቀደስ ብሎም ለማክበር መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ይህንን የነገረ ድኅነት ዐቢይ እውነታ በመግለጥ ሊቁ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በቅዳሴው፡- "ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም ዘለሐኰ ሰብእ ከመ ያግእዞ ለአዳም እምእርዑተ ኃጢአት፤ አዳምን (የሰው ልጆችን) ከኃጢአትና ከፍዳ ቀንበር ነጻ ያወጣ ዘንድ ሰውን የፈጠረበት እጁን ለቀኖት ዘረጋ፡፡ በዚህም ሰውን የፈጠረ ጌታ እጆቹን በመስቀል ላይ ዘርግቶ መከራን ተቀበለ"(200) ብሏል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ትምህርት መሠረት በኋለኛው ዘመን ከወላዲተ አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው የሆነውና መከራ መስቀልን በፈቃዱ ተቀብሎ የታመመው፣ በሕማሙም ከቁስለ ኃጢአታችንና ከደዌ ነፍሳችን የፈወሰን እርሱ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በአምሳሉ አልቆና አክብሮ የፈጠረን አምላከ አዳም፣ እግዚአ አዳም ነው፡፡

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችን በመድኃኔዓለም ክርስቶስ አማካይነት የተፈጸመው አምላካዊ የቤዛነትና የአድኅኖት ሥራ (ሐዲስ ተፈጥሮ) ሰውን በጥንተ ተፈጥሮ በፈጠረው በዚያው አንድ አምላክ ምክር፣ ፈቃድና ሥምረት መከናወኑን በሚገባ ታምናለች፣ ታስተምራለችም፡፡ በዚህ መሠረታዊና ቁልፍ በሆነው የነገረ ድኅነት ትምህርቷም አማካይነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗን ዘወትር በግልጽ ትመሰክራለች፡፡

(200) መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 450፡፡



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. "አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" ተብሎ በቅድስት ኦሪት የተነገረው አምላካዊ ቃል ተስፋ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለው ጥልቅ ግንኙነት ምንድን ነው?
2. መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤልና ቅድስት ኤልሳቤጥ ስለ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት ምን ተናገሩ? ምንስ መሰከሩ?
3. እመቤታችን "ወላዲተ አምላክ" መሆኗ በጉባኤ ኤፌሶን መወሰኑ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ምሥጢራዊ ግንኙነት ያብራሩ፡፡
4. ሊቀ ነቢያት ሙሴ ለጸአተ እስራኤል (ለእስራኤላውያን መውጣት) ምልክት የሆነውን የነበልባልና ሐመልማል ተዋሕዶ በሲና ተራራ ማየቱ ከእስራኤል ዘነፍስ የመዳን ምሥጢር ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
5. ልዑለ ቃል ኢሳይያስ ስለ አማኑኤል የተናገረውን አማናዊ ቃለ ትንቢት ከምሥጢረ ድኅነት ጋር በማገናዘብ ይግለጹ፡፡
6. "ነገረ ድኅነት የትምህርተ ክርስትና ዐቢይ እውነታ ነው" የሚለውን ኃይለ ቃል በአጭሩ ያስረዱ፡፡
7. በነገረ ድኅነት ትምህርት [Soteriology] መሠረት ጥንተ ተፈጥሮ [Creation] እንዲሁም ሐዲስ ተፈጥሮ [Recreation] ማለት ምን ማለት ነው?
8. በነቢዩ ሚክያስ ተስፋ ትንቢት መሠረት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ልደት ከምሥጢረ ስቅለት ጋር ያለውን ግንኙነት ያስረዱ፡፡
9. የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍተ ቅዳሴያት እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ስለመሆኗ ከምሥጢረ ድኅነት ጋር በማገናዘብ የሚያስተምሩትን በአጭሩ ይግለጹ፡፡

በመምህር እንዱዓለም ዳግማዊ /B.Th. M.A/
ሚያዝያ/1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

andudag@yahoo.com
andudag.dagmawi@utoronto.ca